ድምጽ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ቅሬታ መለማመጃ፡ ሁኔታ 1

በአፋር ክልል በሚገኝ አንድ ቀበሌ በተደረገ የድምጽ አሰጣጥ በእድሜ የገፉቸውና ማንበብና መጻፍ የማትችለው ወ/ሮ "ሰ" የመራጭነት ካርድም ሆነ ሌላ ምንም አይነት የመታወቂያ ካርድ ሳትይዝ ለመምረጥ ወደምርጫ ጣቢያው መጣች። በምስክሮች አስመስከራ በመራጭነት መመዝገቧን ብትገልጽም ይህንን የሚያስረዳ ምንም አይነት ሰነድ ማቅረብ አልቻለችም። በእለቱ በምርጫ ጣቢያው በርካታ ሰዎች ለመምረጥ ተሰልፈውና አካባቢውም ተጨናንቆ የነበረ በመሆኑ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊዎች ወዲያውኑ አሰናበቷት። እርስዋም ጎረቤትዋ ለነበረው የአንድ ፓርቲ ወኪል ያጋጠማትን ነገረችው። እርሱም ድምጽ እንድትሰጥ እንደሚረዳት ነገራትና ወደምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይዟት ሄደ። ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አባላት አንደኛው ወ/ሮ "ሰ" ን በግል የሚያውቃትና በቀበሌውም ለረጅም ጊዜ የኖረች መሆኑን የሚያውቅ በመሆኑ የኮሚቴው አባላት ጊዜያዊ ድምጽ እንድትሰጥ ወሰኑ። በዚህም መሠረት ጊዜያዊ ድምጽ እንድትሰጥ ተደርጎ በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ሳይሆን በልዩ ፖስታ እንዲታሸግ ተደረገ። የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም 10 ኪሎሜትሮች ርቆ በሚገኘው ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው የምርጫ ክልል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ዘንድ ሄዳ ጊዜያዊ ድምጹ እንዲቆጠርላት መጠየቅ እንዳለባት ገለጸላት። እርስዋም ይህን ማድረግ አድካሚ እንደሚሆንባት ገለጸች። የፓርቲ ተወካዩ ግን ይህንን እንደሚያደርግላት ገለጸላት።

- ጥያቄ 1 ቅሬታዋን ለመስማት ስልጣን ያለው አካል ማን ነው? የትኛው ፍርድ ቤት (ወይስ አሁንም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስልጣን ነው?)

- ጥያቄ 2 ቅሬታ አቅራቢዋ ቅሬታዋን ማቅረብ የሚኖርባት መቼና የት ነው?

- ጥያቄ 3 ጉዳዩ መወሰን ያለበት መቼ ነው?

- ጥያቄ 4 ይህን አቤቱታ ለማስረዳት ምን አይነት ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል?

- ጥያቄ 5 ይህ ቅሬታ/አቤቱታ እውነት ሆኖ ከተገኘ ምን አይነት መፍትሔ ወይም ዳኝነት ወይም እርምጃ ሊወሰድ/ ሊሰጠው ይገባል?